# ከ**ጌታ** መልእክት

## ለመጋቢዎች (ለፓስተሮች)፣ ለጳጳሳት፣ እና ለክርስቲያኖች

በዶክተር አውጉስቶ ማኩኤንጎ (by Dr. Augusto Maquengo) www.end-times-prophecy.com
**http://www.divinerevelations.info/amharic**

በሜይ 6፣ 2011 ላይ ዶክተር አውጉስቶ ማኩኤንጎ መልእክቱን ከጌታ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ተቀበለ:

መስሪያ ቤት ቢሮ ውስጥ ስደርስ ጌታ በጠዋት ወዲያውኑ ጎበኘኝ። የእርሱ መገኘት ተሰማኝ እና ትከሻዎቼ ላይ አንድ እጅ መጣና እሳት በላዬ ላይ ሲመጣ መስማት እችላለሁ (ይታወቀኛል) እና የ**ጌታ** ድምጽ ሲናገረኝ ሰማሁ እና እርሱ እንዲህ እያለ መናገር ጀመረ:

*ፃፈውና ንገራቸው*:

*ኃያሉ ጌታ አምላክ እግዚአብሔር ለመጋቢዎች (ፓስተሮች)፣ ለወንጌላውያን፣ ለጳጳሳት፣ እና ለሌሎች አገልጋዮች እንዲህ ይላል:- ቁጣዬ ያጠፋችኋል እና በመነጠቅ አትወሰዱም፣ ምክንያቱም እናንተ መንገዴን ትታችኋል እና በጎቼን (ክርስቲያኖችን) የግላችሁ ንብረትና የሀብታችሁ ምንጭ አድርጋችኋል፣ ስለዚህ እኔ ጌታ የንስሃን፣ የመለወጥን፣ ቅጽበታዊ እጅግ በቅርብ ጊዜ መምጣቴን እና የመነጠቅን መልእክት ትተው (በእነዚህ መልእክታት ፈንታ) ከብልጽግና ጋር የተጋቡ እነዚህን መጋቢዎች፣ ወንጌላውያንና አገልጋዮቼን አልወስድም። ለእኔ ሁሉንም ክብርና አክብሮት በመስጠት ፈንታ፣ ፓስተሮች አምላካቸውን እና በእኔ በእግዚአብሔር ሀይል የሰጠኋቸውን ክብር ረስተዋል።* ነቢያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፣ ካህናትም በእነዚህ እጅ ይገዛሉ፣ ሕዝቤም እንዲህ ያለውን ነገር ይወድዳሉ በፍጻሜውስ ምን ታደርጋላችሁ? (ኤርምያስ 5:31)

*እነርሱ የእኔ (የጌታ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ) ቤት የሚሉት፣ የመዝናኛ የቲያትር ቤት እየሆነ መጥቷል፣ እንደ ደራሲያን ፓስተሮችን፣ ጳጳሳትን፣ እና የቤተክርስቲያን አስተናባሪዎችን ይዟል። እነሱ ያለፍርሃት፣ ያለመንቀጥቀጥ፣ ወይም ለእኔ ምንም አክብሮት ሳይኖራቸው በቤቴ ውስጥ እና በመገኘቴ እነሱ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ እና ይዝናናሉ። አህ፣ ክብሬ ቤተመቅደሶቻቸውን ትቶ ሄዷል እና የእኔ መገኘት ቤተክርስቲያኖቻቸውን ትቶ ከሄደ ረጅም ጊዜ ሆኗል። እነሱ ወደ እኔ ወደ አምላካቸው በንስሃ በጸጸት አምርረው ካላነቡና ካላለቀሱ በመነጠቅ አይወሰዱም።*

*አገልጋዮቼ በዓለም ተበላሽተዋል እና እነርሱ አሁን እጅግ በበለጠ መልኩ (በጥልቀት) የዓለምን የፓለቲካ ዘይቤ (አስተሳሰቦች) ቤተክርስቲያን ውስጥ ለማስተዋወቅ እቅዶችን እያደረጉ ናቸው። እነሱ የቫለንታይን ቀንን ቤተክርስቲያን ውስጥ ያከብራሉ እና አለምአቀፍ የውሽታሞችን ቀን ቤተክርስቲያን ውስጥ ያከብራሉ እና በሀዘን በለቅሶ ቀን: ዛሬ የቀብር ቀን ነው ስለዚህ ጥቁር ከለር ያለው ልብስ እንልበስ ይላሉ። ሁሉም ተበላሽተዋል (ተበክለዋል)።*

*ፓስተሮች፣ ወንጌላውያን፣ እና ጳጳሳት ወደ መሬት መቅሰፍት አደጋ (ስጋት)፣ አሰቃቂ ህመም ሥቃይ፣ እና ውድመት በመሬት መጥቶ ሳለ እነሱ ብዙ የመትረፍረፍ ጊዜያት፣ ነፃ የመውጣትና የባለጸግነት ጊዜ እንደሆነ ትንቢት ይናገራሉ። አገልጋዮቼ ብዙ ከእኔ አይሰሙም። የእኔን መንገድ በመተው (በሚያስተው አካሄድ) ራሳቸውን በዓለም በክለዋል። በጸሎት፣ በፆም እና ቃሌን በጥልቀት በማሰብ እኔን አይፈልጉኝም። እነሱ ፆምና ጸሎት የሚያደርጉት ከእኔ የመፈወስ ስጦታዎችን፣ ተአምራትን፣ እና ትንቢቶችን ለራሳቸው ጥቅም (ትርፍ) ለመጠየቅ ነው። እና እነሱ ይህን እንኳ ይላሉ: ለስብከት መልእክት አዘጋጃለሁ። ስብሰባ አዘጋጃለሁ። ታማኞችን በማማከር ሥራ በጣም በዝቶብኛል። ታማኞችን መጠበቅ (መንከባከብ) የግድ አለብኝ እና ለእኔ* **(ጌታ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ)** *ለበጎቹ ባለቤት ግን ጊዜ የላቸውም። እኚህ ፓስተሮች አይነጠቁም ይላል የሠራዊት ጌታ።* (ስለ መነጠቅ፤ የጌታችንና የመድኃኒታችን **ኢየሱስ ክርስቶስ** ወንጌል ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት **ጌታ አምላክ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ** የተናገረውን እንደጻፈው 24:36-51፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 4:16-17)። *እናንተ ለእኔ ፍርሃት ቢኖራችሁ (እኔን ብትፈሩ)፣ ከዛ ከእንባ ጋር በጸጸት በንሰሃ ልብሳችሁን ገንጥሉ (ቅደዱ)፣ ልባችሁን ገንጥሉ፣ አሳባችሁን ገንጥሉ። እኔ ብሄራዊ የቤተክርስቲያን ንሰሃ፣ ለቅሶና እንባ እፈልጋለሁ። ትቢያ ልበሱና በጸጸት (በንሰሃ) አልቅሱ፣ እና ያለበለዚያ ከእኔ ጋር ወደ ሠማያት አትመጡም።*

*ከአገልጋዮቼ ብልጽግና መልእክታት የተነሳ በጎቼ የበሰበሰ፣ የተመተተበት ምግብ በልተዋል። እነዚህ ፓስተሮች በቤተክርስቲያን ግንባታ ፕሮጀክቶች በወደፊቱ ላይ እያዋሉ ናቸው እና እነሱ እኚህ ሁሉ ፕሮጀክቶች በድንገት በውድመትና በአደጋዎች እንደሚቋረጡ አያውቁም። እኔ ሙሽራዬን ከዚህ መሬት (ምድር) ካተረፍኩኝ (ካዳንኩኝ) በኋላ፣ እኚህ እየተገነቡ ያሉ ሕንፃዎች ወደ ምንም ይለወጣሉ። እኚህ ምንም የማያፈሩ ባዶ ሆነው ሥራ ላይ የዋሉ ናቸው። ንፁህ የሕይወት ቃል፣ እውነቱን በመስበክ ፈንታ ገንዘብ ወጪ በማድረግ ሕንፃ ይገነባሉ። በዛ ፈንታ፣ በንሰሃና በዘላለም ሕይወት ውስጥ የነፍስና የመንፈስን ብልጽግና*

*ሰበኩ። እንግዲህ ጌታ እንዲህ ይላል፣ በየቀኑ የምትፈልገኝን እና ቅዱስ ስሜን የምትፈራውን ሙሽራዬን ምን ያህል ነው የምወዳት!!*

*ሰዓት ተጠናቋል። ሰዓቱ አልቋል። አሁን ሙሽራዬን ከእኔ ጋር የምወስድበት ሰዓት እየመጣ ነው። ከዚህ ድርጊት (ሁኔታ) በኋላ ወዲያውኑ፣ መቅሰፍት ጥፋት፣ አደጋ፣ እና አስከፊ ሥቃዮች፣ ከዚህ በፊት ምድር (እዚህ መሬት) ላይ በፍፁም እንዳልነበሩ ሆነው፣ ሕይወቶችን እና ሕይወቶችን ያጠፋሉ። ጠላቴ ሲቆጣጠር፣ ብዙ ንስሃ አይኖርም፣ እኔን የመፈለጊያ ሰዓት አይኖርም፣ ምክንያቱም ምንም ጸሎት አልመልስም፣ እና ጸጋ ይወሰዳል እና የእኔ ቅዱስ መንፈስ በመሬት ላይ አይሆንም። ጠላት ይቆጣጠራል እና እናንተ ጥርሳችሁን ታፋጫላችሁ እና በልባችሁ፣ በሥቃያችሁና በመሰበራችሁ ታለቅሳላችሁ። አሁን ልቦቻችሁን ስበሩ እና ለንስሃ የፈሰሰ ደም አድርጉት። በዚህ በቀረችው የመጨረሻ ሰከንድ ልባችሁን በንስሃ ቀዳችሁ አውጡ (ቅደዱ)፣ አለበለዚያ አስከፊ ቁጣ እናንተን ያጋጥማችኋል።*

*ግን ይህ ህዝብ የሚያሰቅቅ (የሚያስጠላ) እና አመጸኛ ልብ አለው፤ እነሱ አምጸዋል እና ሄደዋል።* *በልባቸውም። የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ በጊዜው የሚሰጠውን፥ ለመከርም የተመደቡትን ወራት የሚጠብቅልንን አምላካችንን እግዚአብሔርን እንፍራ አላሉም። በደላችሁ እነዚህን አስቀርታለች፥ ኃጢአታችሁም መልካምን ነገር ከለከለቻችሁ። በሕዝቤ መካከል ክፉዎች ሰዎች ተገኝተዋል፤ እንደ አጥማጆችም ያደባሉ፥ ወጥመድንም ይዘረጋሉ ሰዎችንም ያጠምዳሉ። ቀፎ ወፎችን እንደሚሞላ፥ እንዲሁ ቤታቸው ሽንገላን ሞልታለች፤እንዲሁም ከብረዋል ባለ ጠጎችም ሆነዋል። ወፍረዋል ሰብተውማል፥ ክፉታቸውንም ያለ ልክ አብዝተዋል፤ የድሀ አደጎች ነገር መልካም እንዲሆን አልተምዋገቱላቸውም፥ የችግረኞችንም ፍርድ አልፈረዱላቸውም።* (ኤርምያስ 5:24-28)። ***መንገዳችሁን እስካልቀየራችሁና ንስሃ እስካልገባችሁ ድረስ አትነጠቁም ይላል ጌታ።***

*ብዙ ጊዜያችሁን የሚይዙትን ቴሌቪዥን፣ ፊልሞችን፣ እና መዝናኛዎችን ያገቡትን እና ለእኔ ለአምላካችሁ እና ለቃሌ ጊዜ የሌላችሁን አልነጥቅም።*

*እግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን በእሁድ ብቻ እያደረጉ ቁጣዬን በሕይወታቸው ላይ እንዳፈሰስ የሚለማመጡትን አልነጥቅም፣ እና እነሱ፣ እኔ እግዚአብሔር፣ ይህን የማላይና የማላውቅ አድርገው ያስባሉ። በእሁድ፣ ለእረፍት ጊዜያት ያላቸውን ምርጥ ልብሶች ለማሳየት እና ከጓደኞቻቸው ጋር ወሬዎችን ለማውራት ብቻ ነው ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄዱት። የእኔ ቤት የማሕበረሰብ መገናኛ ክለብ (ሶሻል ኔትዎርኪንግ ክለብ) እየሆነ መጥቷል።*

*እኔ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእናንተ ጌታ ከቴሌቪዥን ፊት በልቦለዶችና በሌሎች ነገሮች ላይ ሰዓታትና ሰዓታትን የሚያጠፉትን አልነጥቅም፣ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን እንደ ምርጥ ጓደኛ አድርገው መያዝ ሲገባቸው፣ እነዚህ ነገሮች እንደ አማካሪዎቻችሁ፣ ልቦለዶች፣ እና ሳይንሳዊ ትምህርቶቻችሁ ሆነው ተቀይረዋል።*

*የእኔን ቅዱስ መንፈስ መፈለግ የረሳ እያንዳንዱ አማኝ እና በቃሌ ፈንታ ቲቪና ሌሎች ሰይጣናዊ ሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን እንደ ምርጥ ጓደኛ ያደረጉ የክርስቶስ ተቃዋሚውንና የአውሬውን ምልክት ለመጋጠም (to face፣ ለመገናኘት) ይቀራሉ።*

*ኢጋንንት ቀስ በቀስ ቤተክርስቲያን መሃል ውስጥ በመግባት ስኬታማ ሆነዋል እና ዛሬ ቤተክርስቲያን በቃሌና በእኔ በጌታ ክርስቶስ ጠባይ ፈንታ በኢጋንንታዊ የቲኦሎጂ አስተሳሰቦች ጠባይ ተቀርፀዋል። እንደዚህ አይነት ቤተክርስቲያን ይቀራሉ (አይነጠቁም)።*

*እነዚያ፣ በነውረኛ የልብስ ዲዛይን ገላቸውን እያስተዋወቁና እየሸጡ (እየገበዩ) ያሉ፣ ጡታቸውን እያሳዩና አካላቸውን (ሰውነታቸውን) እያጋለጡ ያሉ፤ ይህ በእርግጥ የዓለም ሞዴል (አርአያ) ነው። እኚህ ክርስቲያኖች አምላካቸው እኔን እንዲህ ይነግሩኛል: እግዚአብሔር፣ አስቀድሜ ልቤን ሰጥቼሃለሁ እና ይህ በቂ ነው። የውጭኛው ክፍሌ ግን፣ ለእኔ ፍቀድልኝ፣ ራሴው እንዳሻሁት እየለበስኩ እንድቆጣጠረው ፍቀድልኝ። እኔ አስቀድሜ ከዓለም ጋር እንድትኖሩ፣ እንድትደሰቱና እንድትቆዩ እንደተውኳችሁ በእርግጥ ይታወቅ። እኔ ቀናተኛ አምላክ እንደሆንኩኝ አታውቁም? እኔ በሁላችሁም እቀናለሁ ግን እናንተ ከዓለም ጋር ተካፈላችሁኝ፣ እኔ በእርግጥ ይህን አልቀበለውም።*

*እኔን አሻንጉሊቱ ያደረገኝ እያንዳንዱ ክርስቲያን እና በአእምሮዋቸው እንዲህ የሚሉትን: ዛሬ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደምንኖርና ያም እንደዛ ባለ ዓለም እንደምንኖር ላለመረዳት እግዚአብሔር በጣም መጥፎ አይደለም። በኖህ ጊዜ፣ ከዛሬ በትንሹ ያነሰ መጥፎ ነበር፣ በሎጥ ጊዜ ከዛሬ በትንሹ ያነሰ መጥፎ ነበር፣ ስለዚህ ንስሃ ግቡ ያለበለዚያ ምንም ይቅርታ / ምክንያት አይኖራችሁም።*

*በተቀደሰው የአምልኮ ቀኔ የሚገዙትን፣ የሚሸጡትን እና ጌሞችን የሚጫወቱትን አልወስድም - እኔን እንድታመልኩኝ መሪዎቻችሁ ያስቀመጡላችሁ የትኛውም ቀን እሁድ ወይም ቅዳሜ ለእኔ ብቻ መሆን አለበት፣ እኔ ጌታችሁ ነኝ። ይህ ቀን ለእኔ ብቻ የግድ መቀደስ አለበት። ሰዎች ጌታቸውና አምላካቸው የሆንኩ እኔን አያከብሩኝም። ለእኔ እንዲህ ይነግሩኛል እና ከእውነተኛ አገልጋዮቼ ጋር እንዲህ ይከራከራሉ: ይህ ህግ ነው ግን እኛ በጸጋ ጊዜ ላይ ነን። ጌታችሁ መከበርና መወደስ አይችልም? ጸጋ ማለት አምላካችሁን የማታከብሩ መሆን ማለት ነው? (ጸጋ ማለት ለአምላካችሁ ክብር የምትነፍጉ መሆን ማለት ነው?) ይህን መልእክት ስታዩ በምትከራከሩበት መንገድ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ከእኔ ጋር በጸሎት እንኳ ትከራከራላችሁ።*

*ውሸታሞችን፣ ትዕቢተኞችን፣ እና እንደ ምርጥ ጓደኛ ዓለማዊ ሰዎች ያላቸው ከንቱ አማኞችን ከእኔ ጋር አልወስድም፣ እና እነሱ ራሳቸውን በዓለም ይበክላሉ። እኔ፣ የእናንተ ጌታ እና አምላክ ከእነሱ (ከዓለማዊ ሰዎች) እንድትለዩና ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ እንዳትጠመዱ በቃሌ አዝዣችኋለሁ። 2ኛ ቆሮንቶስ 6:14-17 አንብቡ።*

*ወደ እውነቱ እና እውነታው ላይ ቃላቸውን የሚጨምሩትን (ከፍ የሚያደርጉትን)፣ አገልጋዮቼንና የእውነት የሚያገለግሉኝንና ቃሌን የሚሸከሙትን ፓስተሮቼን የሚአሙትን እኔ አልወስድም። ከቃሌ የትንቢት ቃል ላይ የሚጨምርና የሚቀንስ ለእርሱ ወዮለት።*

*ይህ የእኔ አቋም ነው፣ ተቀበሉት፣ እና አስቀምጡት፤ ይላል ጌታ።*

*እኔ፣ የሹአህ መሲህ፣ አምላካችሁ እና ሌላ... ሌላ ማንም የለም።*

*ተዘጋጁ፣ ተዘጋጁ፣ በቅርቡ እደርሳለሁ!*

[**ጌታ አምላክ መድኃኒት የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ**:-

ስለ ትንሣኤ ሙታን ግን። እኔ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን? የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም። Matthew 22:31-32

ኢየሱስም እንዲህ አላቸው። የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም። (ዮሐንስ 6:35)

ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው። John 6:51

ደግሞም ኢየሱስ። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው። John 8:12

የላከኝ አብ ከእኔ ጋር ነው እንጂ ብቻዬን አይደለሁምና እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው። John 8:16

በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ። John 9:5

ኢየሱስም ደግሞ አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ። John 10:7

በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል። ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ። መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል። John 10:9-11

መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ። John 10:14-15

ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ። John 10:17-18

እኔና አብ አንድ ነን። John 10:30

ኢየሱስም። ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን? አላት። Joh 11:25 -26

ኢየሱስም። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። John 14:6

እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል። እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ። John 14:10-11

እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው። ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል። John 15:1-2

እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል። በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል ይደርቅማል፤ አነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሉአቸዋል፥ ያቃጥሉአቸውማል። በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል። ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል። አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ። እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ። እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም። እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ። ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፥ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና። እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፥ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ። እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ። ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ እወቁ። ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል። ባርያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ። እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው እንደ ሆኑ ቃላችሁን ደግሞ ይጠብቃሉ። ዳሩ ግን የላከኝን አያውቁምና ይህን ሁሉ ሰለ ስሜ ያደርጉባችኋል። John 15:5-21

እኔ ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔም ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው። John 17:14

ጲላጦስም። እንግዲያ ንጉሥ ነህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ። እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው። John 18:37

ከገናናው ክብር። በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና፤ እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን። 2Peter 1:17-18

ተፈጽሞአል። አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ። Revelation 21:6

አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። Revelation 22:13

እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላከሁ። እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ። Revelation 22:16

መንፈሱና ሙሽራይቱም። ና ይላሉ። የሚሰማም። ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ። በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤ ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል። ይህን የሚመሰክር። አዎን፥ በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን። Revelation 22:17-21 ]

በእስራኤል አምላክ በሠራዊት ጌታ፣ በነገሥታት ንጉሥና በጌቶች ጌታ በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እርዳታ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተረጎመው፣ ቶማስ ጌታቸው። Translated to Amharic by Thomas Getachew Tuta, hithomasgetachew@gmail.com